የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መ.ኢ.ሶ.ን./ ልሳን

ቁጥር 45
ነሀሴ 10፣1968

የቀለበሱ ሙከራዎችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል

በአገራችን፣ከሁለት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ፣ብዙ ውጣ ውረዶችን የተጓዘ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ዛሬም ይካሄዳል፡፡ግቡን አልመታም፣በፀረ አብዮት ኃይሎች አሸናፊነትም አልተገታም፡፡እንደዚህም ሆኖ በነዚህ የትግል ጊዜያት ከፍተኛ ድሎች ተገኝተዋል፡፡የሚቀሩን ድሎችም ብዙ ናቸው፡፡እስካሁን የተገኙ ድሎች በበኩላቸው ለአብዮታዊው እንቅስቃሴ መቀጠል በጣም ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡ነገር ግን፣እስከዛሬም ድረስ በነዚህ ድሎች ተጠቅሞ ለድሎቹ ዋስትና ለመስጠትና የሚቀሩትን መሰረታዊ ድሎች ለመቀዳጀት ትግሉን ከከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ አልተቻለም፡፡የድሎቹ መጠበቅ ሆነ የትግሉ በከፍተኛ ደረጃ መቀጠል አሁንም አስተማማኝ ዋስትና የለውም፡፡ጭቁኖችና ተራማጆች ትግላቸውን አፋፍመው አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ የሚታገሉትን ያህል የሕዝብ ጠላቶችም ኃይላቸውን ሰብስበው አብዮቱን ለመቀልበስ በመታገል ላይ ናቸው፡፡በሌላ አነጋገር፣ዛሬ ጭቁኖችም ጨቋኞችም ለተቃራኒ ግቦች ወሳኝ ዝግጅት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡እንዲያውም ከጭቁኖች ይልቅ ጨቋኞች የተሟላ ዝግጅት ይዘው ለመቅረብ በመራወጥ ላይ ናቸው፡፡የዛሬው አብዮታዊ ትግል ከነዚህ ሁለት ተፃራሪ ወገኖች በየትኛው አሸናፊነት ለጊዜው እንደሚዘጋ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሆነበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡ከታሪክ አንፃር ሲታይ የሰፊው ሕዝብ ማሸነፍ የማይቀር ነገር ነው፡፡ይህ ግን ፀረ ሕዝብ ኃይሎች አሸንፈው ለተወሰነ ጊዜ የሕዝቡን ትግል ሊቀለብሱ አይችሉም ማለትን አያመለክትም፡፡የጭቁኖች የትግል ታሪክ የድል ብቻ ሳይሆን የመሸነፍም ገጾች አሉት፡፡የኢትዮጵያ ሀቀኛ ተራማጆችና ጭቁኖች የምንገኝበት ሁኔታ ይኸው መሆኑን መረዳት አለብን፡፡

የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 40 ላይ፣የደርጉ መለስተኛ ፕሮግራም መውጣት ለሰፊው ሕዝብ ትግል አመቺ ሁኔታ የመፍጠሩን ያህል ጠላቶቻችንም ከመቸውም የበለጠ ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ያስገድዳቸዋል ብለን ነበር፡፡ከመለስተኛ ፕሮግራሙ ወዲህ ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህንን ሀቅ በሚገባ ያረጋግጣል፡፡የተለያዩ መለኮች ይዘው የሚቀርቡት የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በየፊናቸው ፀረ አብዮት ትግላቸውን አፋፍመዋል፡፡ደርጉ ከቀኝ ጉደል ወገን በመለየቱ፣ኢምፔሪያሊስቶች የኢትዮጵያን ፀረ አብዮት ኃይሎች ለማስተባበርና ለመርዳት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ተነሳስተዋል፡፡እንግዲህ፣የፀረ አብዮት ኃይሎች ዝግጅትና ትግል በጣም ከፍ እያለና እየተጠናከረ መጥቷል ማለት ነው፡፡

በአገር ውስጥ፣ጥቅማቸው የተነካና በስጋት አብዮቱን የከዱ ነጋዴዎችና ከበርቴዎች የአገሪቷን የኑሮ ችግር ለማባባስና ኢኮኖሚውን የበለጠ ለማቃወስ ዛሬ በየቦታው በመጠኑ መጋለጥ የጀመሩትን አሻጥሮች በማካሄድ ላይ ናቸው፡፡የሚሰሩት አሻጥር በመጠኑ ተጋለጠ እንጂ አሻጣሪዎቹ አልተወገዱም፡፡ዛሬም እነሱ በሚሰሩት አሻጥር የሚፈጠረው የኑሮ ችግር አልቀነሰም፡፡የሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ቀውስም አልተስተካከለም፡፡የተባባሰ የኑሮ ችግር፣የተተራመሰ ኢኮኖሚ ለአብዮት ቀልበሳ ጥሩ አካባቢ ስለሚፈጥር ወደፊትም ሙሉ በሙሉ እስካልተጋለጡና እንደ አንዱ የአብዮቱ ጠንቅ እስካልተመቱ ድረስ ይህን ፀረ አብዮት ስራ አያቆሙም፡፡እንዲያውም ለነዚህ ፀረ ሕዝብ ክፍሎች የሚሰጠው ፀረ አብዮታዊ የትግል ድርሻ ዛሬ በተሰማሩበት የኢኮኖሚ አሻጥር በኩል ስለሆነ፣ከሲአይኤ በሚጎርፍላቸው ገንዘብ አስፈላጊ ሸቀጦችን ገዝተው መደበቅ፣ሸማቹ የሚፈልገውን ሸቀጥ ማሳጣት፣በዚህም የሰፊውን ሕዝብ ችግር ማባባስ ዓይነተኛ ተግባራቸው ይሆናል፡፡

ለፊውዳሊዝምና ለኢምፔሪያሊዝም ጥቅም ማስጠበቂያ የቆመ ቢሮክራሲ በምንም ተዓምር የሰፊው ሕዝብ አብዮት ማራመጃ መሳሪያ ሊሆን አይችልም፡፡የኢትዮጵያ ቢሮክራሲ ቁንጮው ላይ በመጠኑ ቢመታም እስካሁንም በበቂ ያልተነካ የአብዮት ጠላት ነው፡፡ዛሬም ከአብዮቱ ተላላቅ እንቅፋቶች አንዱ ይኸው ከኃይለ ሥላሴ የተወረሰው ቢሮክራሲ ነው፡፡ቢሮክራሲው በሺህ ድሮች ከአሮጌው ስርዓት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በአሰራሩ ሁሉ የዚህን አሮጌ ስርዓት መደምሰስ ቀርቶ በቅጡ መሻሻል ለማስቀረት ይጥራል፡፡በገጠር፣ፀረ አርሶአደር እርምጃዎች በመውሰድ፣በድብቅና በግልጽ ከአርሶአደሩ ጠላቶች ጋር በማበር የአብዮቱን ሂደት ለማደናቀፍ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ነው፡፡ተላላቅና አድሃሪ ቢሮክራቶች፣ፀረ አብዮት ኃይሎች በኢምፔ

ሪያሊዝም አስተባባሪነት ደርጉን ገለብጠው ሊያስቀምጡ ለሚፈልጉት አሻንጉሊት ፀረ ሕዝብ መንግስት፣ለመሪነት የሚታጩ ናቸው::በኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት የኢትዮጵያን አብዮት ጠላቶች የሚያግዝና የሚመራ ኃይል የሚፈልቀው ከቢሮ ከበርቴው ለመሆኑ ምንም ጥርጥር አይኖርም::ቢሮ ከበርቴው ከውስጥና ከውጭ አድሃሪዎች ጋር በገባው ፀረ አብዮት ቃል ኪዳን መሰረት፣በሥልጣኑ ተጠቅሞ የአብዮትን እድገት ሊገታ ይፍጨረጨራል::በስውርና በዘወርዋራ አሻጥር ትግሉን ለያደናቅፍ ያሴራል::የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ወደፊት ይገፋ ዘንድ የቢሮክራሲውን አሻጥር እየሰባበረ መሄድ አለበት::ሰፊው ሕዝብ የድሉና የእድሉ ባለቤት መሆኑ የሚረጋገጠውም በነዚሁ ትግሎች ውስጥ አልፎ የዛሬውን ቢሮክራሲ ፈረካክሶ በመጣል በቦታው የራሱን ሕዝባዊ አስተዳደር ሲገነባ ብቻ ነው::የአብዮቱ ከግቡ መድረስ ዋስትና የሚኖረውም ያን ጊዜ ብቻ ነው::ይህ መታወቅ ያለበት የአብዮት ሀቅ ነው::ስለዚህም የዛሬውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ለመቀልበስ ከሚታገሉት ጠላቶች አንደኛው አሁንም ከሥልጣን ያልተወገደው ቢሮ ከበርቴ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል::

ከመንግስት ሥልጣን ከሞላ ጐደል የተወገደው፣የኢኮኖሚ ብዝበዛ መሰረቱን የተነጠቀው የፊውዳሉ መደብ እስከዛሬም ድረስ በተያያዘው አብዮታዊ እሳት ሙሉ በሙሉ አልተቃጠለም::ያመለጡ መሳፍንት ከውጭ አድሃሪዎች የመሳሪያ እርዳታ በመሰብሰብ ላይ ናቸው::በሲአይኤና በሌሎችም ኢምፔሪያሊስቶች እርዳታ ፋሺስታዊ ድርጅታቸውን በማጠናከር ላይ ናቸው::በውስጥ የሚገኙ ወኪሎቻቸውም በየቦታው ፀረ አብዮት አመፃቸውን በማቀጣጠል ላይ ናቸው:: ዛሬም ቢሆን የብዙ ክፍለ ሀገር አርሶ አደሮች ከመሬት ከበርቴዎች ጥይት እፎይ አላሉም::ከጥይቱም ሌላ አርሶአደሩን አወናብደው ከጎናቸው ለማሰለፍ የሚያደርጉት ጥረት በቀላሉ የሚታይ አይደለም::ፋታ አግኝተው ኃይላቸውን ባጠናከሩና የትጥቅ ትግላቸውን በየጊዜውና በየቦታው በለኮሱ ቁጥር በጭቁን ሕዝቦች ትግል ላይ የሚጥሉት አደጋ ቀላል አይደለም::

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ኢምፔሪያሊስቶችን መሪነት ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ፣የጭቁን ሕዝቦችን ትግል ለመቀልበስ፣አድሃሪ ስርዓቶችን ለመጠበቅ እጁን ያላስገባበት አገር በዓለም ላይ የለም::ከነዚህም በርከት ባሉ አገሮች/በኮሪያ፣በኮንጐ፣በቬየትናም፣በላኦስ፣በካምቦዲያ.../ቀጥተኛ ወረራዎች በማድረግ ከፍተኛ የግድያና የማጥፋት ጦርነቶች አካሂዷል::ዘር ዘር በጭቁኖች አብዮታዊ አመጽ ተደቁሶ ሀፍረት ተከናንቦ ከነዚህ አገሮች ከመባረር ባይድንም በነዚህ ሕዝቦች ላይ ያደረሰው እልቂትና መከራ እጅግ ከባድ ነበር::በሌላ አንፃር፣በአብዛኛዎቹ አገሮች የሕዝቦችን ትግል ለመደምሰስና ፀረ ሕዝብ አገዛዞችን ለመጠበቅ የተጠቀመበት ዘዴ ቀጥተኛ ወረራ ብቻ አልነበረም::ባንድ በኩል በየአገሩ ያሉ ቡችሎችን እስከአፍንጫቸው በማስታጠቅ፣በሌላ በኩል ደግሞ ሲአይኤ በተባለው የስለላና የነፍስ ገዳይ ድርጅቱ አማካይነት ሕዝባዊ ትግል ገፍቶ አሻንጉሊት መንግስቱን በሚያርበደብድበትና ተከታይም በሚጥልበት ጊዜ ፋሺስታዊ መፈንቅለ መንግስት በማውጠንጠን የጭቁኖችን ትግልና እድገት የገታበት ቦታ ጥቂት አይደለም::በኢራን፣በኢንዶኔዚያ፣በብራዚል፣በቺሊ...ና በርከት ባሉ ሌሎች አገሮች የተቋቋሙት ፋሺስታዊ አገዛዞች በሙሉ የሲአይኤ ፍጡሮች ናቸው::እንደነቬየትናም በቀጥታ ወረራ ባይሆንም፣ሲአይኤ በመፈንቅለ መንግስት ባመጣቸው አገዛዞች አማካይነት በነዚህ አገሮች ሕዝቦች ላይ ከፍተኛ ፍጅት ስቃይና በደል ተፈጽሟል፣እየተፈጸመም ነው:: .በቀጥተኛ ወረራ የጭቁን ሕዝቦችን ትግል ለመደምሰስ ባደረጋቸው ተደጋጋሚ ሙከራዎች በደረሰበት ኪሳራና ውርደት፣በተለይም የዓለም ተራማጅና ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ ከፍተኛ ተቃውሞ ስላለበት፣በዛሬዋ ዓለም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ያተኮረው በሲአይኤ አማካይነት አብዮት ለመቀልበስ በሚደረግ መፈንቅለ መንግስት ላይ ነው::ወረራው ከጥያቄ ውጭ ሆኗል ለማለት ባይሆን፣በቅድሚያ የሚመከረው የመፈንቅለ መንግስት ሴራ እንደሆነ ለመጠቆም ያህል ነው::በየአቅጣጫው በጭቁኖች ትግል ተወጥሮ የሚያጣጥረው ኢምፔሪያሊዝም የጭቁኖችን ትግል ለመደምሰስ ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም አይመለስም::

እንግዲህ፣ኢትዮጵያም ኢምፔሪያሊስቶች ከብዙ አመታት ጀምሮ በቁጥጥራቸው ስር አውለው ሲበዘብዟትና ሲጨቁኗት የቆየች አገር በመሆኗ፣በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ነፃነቷን እንዴት ቀዳጀ፣ከርሱ ተጽእኖ እንዴት ተላቀቀ በፍፁም አይፈለግም::

ባለፉት ሁለት ዓመታት የተካሄደው እንቅስቃሴ በገቢር ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት ቢኖረውም፣ኢምፔሪያሊዝምን በማያዳግም ሁኔታ ካገራችን ገጽ ሊያጠፋ የሚችለው የእንቅስቃሴ ደረጃ ገና ልንደርስበት የተቻኰልነው ነው:: ዐታደራዊው ደርግም በመሰረቱ አንዳንድ ፀረ ኢምፔሪያሊስት እርምጃዎች ቢወስድም፣ከሞላ ጐደል ግልጽ ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋሞች ማሳየት ከጀመረ ጊዜው ሩቅ አይደለም::ስለዚህም፣ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ጭቁኖች ኢምፔሪያሊዝምን ካገራቸው ምድር ሳያባርሩ ነፃነታቸውን ለማግኘት እንደማይችሉ ተረድተው ለዚህ ትግል መዘጋጃቸው ጊዜ በመሆኑ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ትግላቸው በርግጥ እርሱን የመደምሰሻ ኃይል ሳያገኝ ባጭሩ ሊቀጨው ሮይበልጥ ተነሳስቷል::በሌላ በኩል ደግሞ፣ደርጉ ከንግዲህ በመለስተኛ ፕሮግራሙ የወሰናቸውን ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋሞች በሥራ መተርጐም ከቀጠለ፣ኢምፔሪያሊስቶች በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም-ከድሮው ይበልጥ ዛሬ ..ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም.. ማለቱ አልቀረም::እንግዲያውም፣ከዚህ በታች በምንመለስበት

የመንግስት ግልበጣ ሙከራ እንደምና የው፣ የአሜሪካን አምፔሪያሊዝም እስካሁን እንዳደረገው በከሸከሸ የኩዴታ ሙከራ ሳይሆን፣ ወይንም ደርግንም አለሁልህ ጠላቶችንም አለሁላችሁ እያለ ሳይሆን በተፋፋመና በተጠናከረ ዝግጅት ደርግን ለመገልበጥ ወስኗል፡፡ ሰሞኑን የአምፔሪያሊስት ጋዜጦችና የዜና ማሰራጫዎች የኢትዮጵያን አብዮትና ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከሰፊው ሕዝብ ጎን የተሰለፈውን ደርግ በማጥላላት የሚያካሂዱት ዘመቻ በቺሊ አሌንዴን ለመገልበጥ የፕሮፓጋንዳ ዝግጅት ሲያደርጉ የነበረውን ሁኔታ ያስታውሰናል፡፡

በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል በየካቲት/66 ሲቀጣጠል ባንድ ላይ የተነሳው ኃይል ሁሉ ዛሬ አብሮ የለም፡፡ የየካቲት እንቅስቃሴ ተጀምሮ የአክሊሉ ካቢኔ በሕዝቡ ትግል ሲወድቅ ከተከፋፈሉት የገዥ መደቦች ውስጥ የእንዳልካቸው ወገን ሳይቀር ደስ ብሎት ነበር፡፡ እነመንገሻ ሥዩምም አሁን ሲያወሩ የየካቲት እንቅስቃሴን እንደተጀመረ መደሰታቸውን ይገልፃሉ፡፡ በዘረፋ ላይ ከተጣሉዋቸው የመደብ አቢሉቻቸው ከፊሉን አስወግዶ የሚገታ እንጂ እንደዚህ ገፍቶ መጥቶ ጉዱ የሚሰራቸው እንቅስቃሴ አልመሰላቸውም ነበር፡፡ ከሰፊው ሕዝብ ጋር በኃይለ ሥላሴ የአፄ አገዛዝ ላይ ክንዱን ያስተባበረ የንዑስ ከበርቴው የተወሰነ ክፍልም እንቅስቃሴውን ወደ መጀመሪያው ላይ በሙሉ ድጋፍ፣ ከዚያም በጥርጣሬ ሲከተል ቆይቶ በመደብ ጥቅም መነካት፣ በትንፋ ቁራጭነት ከአብዮቱ እየተራገፈ ቀርቷል፡፡ ከአብዮቱ ሰፈር ወጥቶ የአብዮት ጠላቶች ሰፈር ተደባልቋል፡፡ ''ኢህአፓ'' ብሎ እራሱን በሚጠራ የከሃዲ ምሁራን ጥርቅም የሚመራው ይህ ክፍል ዛሬ ከቀንደኛ ጠላቶቻችን ባላነሰ ትግል የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ሽር ጉድ በማለት ላይ ነው፡፡ የሌሎቹ የሕዝብ ጠላቶች፣ ሰፊው ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው በመሆኑ በምንም ዓይነት ዘዴ ሰፊው ሕዝብ እንዲተባበራቸው ለማድረግ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ፣ ሰፊው ሕዝብ ተወናብዶ በራሱ አብዮት ላይ እንዲያምጽ፣ ዛሬ በታሪክ አጋጣሚ በጊዜያዊ ደረጃ በጎኑ የቆመውን ደርግ የመጀመሪያው ጠላት ተደርጉ እንዲወሰድ ውዥንብር እንዲነዛ፣ በዚህም ደረጃ ሁኔታውን ለግልበጣ እንዲያመቻች የትግል ድርሻ የተሰጠው ለዚሁ ከሃዲ የንዑስ ከበርቴ ክፍል ነው፡፡

የሕዝቦች ትግል ረዥምና መራራ የሚሆነው ከሌሎቹ ጠላቶቻቸው ጋር መጋጠም ስላለባቸው ብቻ ሳይሆን፣ እነርሱን መስለው ተደብቀው ትግሉን ከውስጥ ለማዳከም ከሚጥሩ አስመሳይ ተራማጆችም ጋር የሞትና የሽረት ትግል ማድረግ ስላለባቸው ነው፡፡ በመደብ ጠርነቱ፣ ፊት ለፊት ከሚጋጠም ጠላት ይልቅ አብሮ የተሰለፈ መስሎ ከጀርባ የሚወጋ የበለጠ አደገኛ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ዛሬ፣ ትግሉን ስንጀምር ፊት ለፊት ከገጠምነው ጠላት ጋር ብቻ ሳይሆን አብረውን ጀምረው ፊት ለፊት በገሀድ ገጥመውት እንዳንሸነፍ ከጀርባ የሚወጉንን 'የውስጥ አርበኞች' ሳናውቅና ሳናጋልጥ አብዮታችን ያለበትን ችግርና ከግቡ የሚደርስበትን መንገድ ልንረዳ በፍፁም አንችልም፡፡

ወታደራዊው ደርግ የቀድሞ ገዥ መደቦችን ሥልጣን አስለቅቆ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት እንዳቋቋመ በአገራችን የመደብ አሰላለፍ ለውጥ ተከተለ፡፡ የቀድሞው የትግል ስልት መቀየር ያለበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ መንግስትን ከተቃዋሚ ጋር ሁሉ መተባበር አብዮታዊ ግዴታ ነበር፡፡ በደርግ ዘመን መንግስትን ከተቃዋሚ ጋር ሁሉ መተባበር ግን ከቀድሞ ገዥ መደቦች ጋር መተባበርን ሊያስከትል የሚችል የትግል ስልት ሆነ፡፡ ምክንያቱም ደርጉን ለመተካት የሚፈልጉት ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች — ሰፊው ሕዝብና ጠላቶቹ — ሆኑ፡፡ በተለይ ተከታታይ የደርጉ ተራማጅ እርምጃዎች ከመጡ በኋላ በሕዝብ ጠላቶች በኩል ደርጉን ለመተካት የሚፈልገው ወገን በረከተ፡፡ ደርጉን ለመተካት በሚፈልጉ ሁለት ተፃራሪ ወገኖች መሃል የነበረው/ያለው/የኃይል ሚዛን ለጠላቶች ያመዘነ ነበር፡፡ ደርጉ በፈለገው ምክንያት ፊትም ሆነ ዛሬ ሲወድቅ ሊተኩት የሚችሉት የሕዝብ ጠላቶች ነበሩ/ናቸው፡፡ የአብዮቱ ጠላቶች ከየካቲት እንቅስቃሴ ተምረው ስልጣን ያስለቀቋቸውን ደካማ ለማስወገድ ከፍተኛ ዝግጅት አድርገዋል፡፡ ሰፊው ሕዝብ ግን በየካቲት እንቅስቃሴ ሥልጣን እጁ ለማስገባት ያስቻለውን ደካማ አላስወገደም፡፡

የመንግስት ሥልጣን ጉዳይ የጉልበት ጥያቄ ነው፡፡ የበለጠ የተዘጋጀና የተደራጀ ይወስዳታል እንጂ በአብ ሰጪ ማንም እጅ አትገባም፡፡ ሃቀኛ ተራማጆች፣ ባንድ በኩል የሰፊውን ሕዝብ ደካማ ተረድተው፣ በሌላ በኩል ሰፊው ሕዝብ ሥልጣን ካልያዘ መሰረታዊ ችግሮቹ ዋስትና ባለው መንገድ እንደማይፈቱ ተገንዝበው፣ ሰፊው ሕዝብ ለመንግስት ሥልጣን የሚያበቃትንና ሊዘለሉ የማይችሉ ዝግጅቶችን እንዲያሟላ፣ ማለትም እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳቸውን አፋፋሙ፡፡ በዴሞክራሲያ ግንባር ቀደምነት የሚመራው የከሃዲ ንዑስ ከበርቴ ክፍል ግን፣ መጀመሪያ ደርግን እንጣል፣ አስቀድመን ጊዜያዊ ''ሕዝባዊ'' መንግስት እንመስርት፣ ንቃተ ድርጅቱ ትጥቁ ከዚያ በኋላ በየደረጃው ይሟላል በሚል ፀረ አብዮት ቅስቀሳ ላይ ተሰማራ፡፡ እንግዲህ፣ ሰፊውን ሕዝብ ከጠላቶች አስተባብሮ ደርግን ለመጣል የተደረገው የከሃዲ ምሁራን ሙከራ ''ጊዜያዊ 'ሕዝባዊ' መንግስት'' በሚለው መፈክር አካባቢ ነበር፡፡ ባንድ በኩል፣ ንቃተ ድርጅትና ትጥቁ ከ'ጊዜያዊ ሕዝባዊ' መንግስት በኋላ ይመጣል የሚለው ቅስቀሳ፣ ሰፊው ሕዝብ ሳይነቃ፣ ሳይደራጅና ሳይታጠቅ ''እየታገለ'' በነቃ፣

በተደራጁና በታጠቁ ጠላቶቹ የሚያስመታው ቅስቀሳ ነው::በሌላ በኩል ደግሞ፣ሰፊው ሕዝብ እነዚህን ሶስት መሰረታዊ ዝግጅቶች ሳያሟላ የፈለገውን ያህል ''ቢታገል'' የተገራን ፍሬ ጠላቶቹ ይሰበስቡሉ እንጂ እርሱ ሥልጣን ሊይዝ አይችልም::በዚህም ምክንያት ሰፊው ሕዝብ የመንግስት ሥልጣን ለመያዝ ቢችል ''ዝግጅቱን ተቱ ሥልጣን ለመያዝ ታገል'' ማለት''ይበልጥ የተዘጋጁትን ጠላቶችህን ሥልጣን ለማስያዝ ታገል'' ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም::ለዚህ ነው ''ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት'' የሚለው መፈክር ሰፊውን ሕዝብ ከጠላቶቹ ጉን እንዲሰለፍ ለማወናበድ የሚሰነዘር መፍክር ነው የምንለው::የሕዝብ ጠላቶችም ይህንኑ ጠንቅቀው በመረዳታቸው ይህን ቀልባሽ መፈክር አንግበው ተነስተዋል::

ሰፊው ሕዝብ ተወናብዶ ከጠላቶቹ ጉን እንዲሰለፍ ለማድረግ እነዲሞክራሲያ የተጠቀሙበት ሌላኛው ቅስቀሳ ባጠቃላይ በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለውን ቅራኔ የሚጋለከትና ''ተለይም''ደርጉ ፋሺስት ነው'' የሚለው ነው::

''ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፈነ'' ስለሚሉት ''ፋሺዝም''በሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 43 ላይ በሰፊው የተቸገበት ስለሆነ ለጊዜው እዚህ ላይ በዝርዝር አንመለስበትም::ሆኖም ጥያቄውን ከሌላ አንፃር ባጭሩ እንመለከተው::በአንድ ጊዜ ሊኖር የሚችለው አንድ ዋና ቅራኔ ብቻ ነው::ይህ አንድ የማርክሲዝም ሕግ ነው::በኢትዮጵያ፣ደርጉ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ዋናው ቅራኔ ከሆነ፣/ደርጉ 'ፋሺስት' ነው ከተባለ ደግሞ በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ የግድ ዋነኛው መሆን አለበት::/ ሌሎች በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ውስጥ ያሉት ቅራኔዎች በሙሉ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች ናቸው ማለት ነው::በዚህ ዋና ቅራኔ መፈታት ጥቅም የሚያገኙ ኃይሎች ሁሉ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔያቸቸውን አቻችለው ይህን ዋና ቅራኔ ለመፍታት በጋራ መታገል አለባቸው::ለምሳሌ፣በበሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጊዜ ዋናው ቅራኔ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ባንድ በኩልና በሰፊው ሕዝብ በሌላ በኩል መሃል ያለው ቅራኔ ነው::በገዐስ ከበርቴውና በወዛደሩ መሃል ቅራኔ አለ::ነገር ግን በዚህ ዋና ቅራኔ መፈታት ሁለቱም ጥቅም ስለሚያገኙ በመሃላቸው ያለውን ቅራኔ ለጊዜው አቻችለው ዋናውን ቅራኔ ለመፍታት ይታገላሉ::እንግዲህ፣በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ከሆነ፣ከደርጉ ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚገኙ ኃይሎች ሁሉ መተባበር አለባቸው ማለት ነው::ከደርጉ ጋር በቅራኔ ውስጥ ከሚገኙት ኃይሎች ውስጥ ደግሞ የቀደሞ መሳፍንት እነመንገሻ ሥዩም/ነጋ ተገኝ...ይገኙበታል::ስለዚህም፣ሰፊው ሕዝብ ከነዚህ መሳፍንት ጋር ተባብሮ ደርጉ ላይ መነሳት አለበት ማለት ነው::ከሃዲ ምሁራን ይህን በግልጽ ለመናገር እንደማይደፍሩና ለመካድም እንደሚሞክሩ የታወቀ ነገር ነው::ነገር ግን፣በደርጉ ላይ ካላቸው አቋም የግድ ሊ"ተል የሚችለው መደምደሚያ ከላይ ያለው ነው::እንደኛ፣በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ከሆነ የግድ በዚህ ቅራኔ መፈታት ጥቅም ያላቸው ሁሉ መተባበር አለባቸው::ሁለተኛም፣ደርጉ ''ፋሺስት'' ከሆነ፣ተደጋግሞ እንደተነገረው ከመሳፍንት ጋር ሳይቀር ተባብሮ ይህን ''ዋና ጠላት'' መታገል ያስፈልጋል::የቻይና ሕዝቦች ከፊውዳሊስቶች፣የቪየትናም ሕዝብ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ሆነው ፋሺስቶችን የታገሉት ፋሺዝም ስለነገሰ የቀደመው ዋና ቅራኔ ወደሁለተኛ ደረጃ ቅራኔነት በመዞሩ ነው::ለምሳሌ፣በቻይና በፊውዳሊዝምና በሰፊው ሕዝብ መሃል የነበረው ዋና ቅራኔ በፋሺዝም ምክንያት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ በመለወጡ ነው::ደርጉ ''ፋሺስት ነው'' የሚለው የፈጠራ ቲዎሪ የተነሳውም ለዚሁ ግብ ነው::ማለትም፣ሰፊውን ሕዝብና ደመኛ ጠላቶቹን ''በፀረ ፋሺስት ግንባር'' ለማስተባበር ነው::ሰፊውን ሕዝብ ከጠላቶቹ ጋር ለማስተባበር የነሡት ውዥንብር ለጊዜው ባይሳካም፣'ኢህአፓ' ከሃዲዎች እራሳቸውን ''ፀረ ፋሺስት'' ብለው ከሚጠሩ ካገር የኰበለሉ ፋሺስቶች ጋር እንደሚተባበሩ በበኩላችን ምንም ጥርጥር የለንም::ዛሬማ 'ኢህአፓ' የውጭ ተጠሪ ነኝ የሚለው የፋሺስት ወጣቶች ድርጅት ''በኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት ውስጥ ያሉ አድሃሪዎች ይውደሙ'' የሚል መፈክር አንግበ ተነስቷል::''የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት''የነመንገሻ ሥዩም/አስፋ ወሰን ድርጅት መሆኑ እየታወቀ ይህን መፈክር ማንሳቱም እነ አስፋ ወሰን/መንገሻ ሥዩም መሃል ''ስርገው የገቡ'' አድሃሪዎችን በማውገዝ ''ለተራማጆቹ'' የዚህ ድርጅት አባሎች የትብብር እጅን መዘርጋቱ ነው::የኢዲህ ሰዎችም 'ከፀረ ፋሺስት ተራማጆች ጋር እንተባበራለን፣ከነአስፋ ወሰን ጋር ግንኙነት የለንም ብለዋል:: አድሃሪዎች በ'ኢህአፓ' የውጭ ተጠሪ ጥያቄ አማካይነት ከኢዲህ ውስጥ 'ከተገለሉ' ደግሞ፣የነመንገሻ ሥዩም ዓይነት ''ተራማጆች''ና 'ኢህአፓ' ''ፀረ ፋሺስት ግንባራቸውን''ለማቋቋም የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም ማለት ነው::

ደርጉን ''ፋሺስት'' ነው በማለት እነ መንገሻ ሥዩምን ደጅ ለመጥናት ከተነደፈው ስያሜ ሌላ፣'ኢህአፓ' አድሃሪዎች ሕዝቡና ጠላቶቹ እንዲተባበሩ የተጠቀሙበት ሌላ ዘዴ፣ደርጉ በወሰዳቸው አድሃሪ እርምጃዎች ላይ በተናጠል ማተኮር ነው::ደርግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ የነበረው እረማመድ ቅራኔ የተሞላው ነበር::ቅራኔያዊ በመሆኑም የደርጉን ሚና ለመረዳት ከአንድ አንፃር ብቻ ማየት አይቻልም::ለምሳሌ፣የኢትዮጵያን አርሶአደር

መሰረታዊ ጥያቄ የሆነውን መሬትን የሕዝብ ያደረገ አዋጅ አለ::በሌላም በኩል የአርሶአደሩን ትግል ያደናፍፉ የወላዋይነትና አድሃሪ እርምጃዎች አሉ::በተራማጅ አዋጁ ላይ ብቻ አተኵሮ እነዚህን ወላዋይና አድሃሪ እርምጃዎች መርሳት አድርባይነትና አርሶ አደሩ እነዚህን አድሃሪ እርምጃዎች ለመቋቋም ማድረግ ካለበት ትግል ማዘናጋት ነው::ተራማጅ አዋጁን ቸለ ብሎ በወላዋይና በአድሃሪ እርምጃዎቹ ላይ ብቻ ማተኰር ደግሞ በነዚህ ወላዋይና አድሃሪ እርምጃዎቹ ሰበብ ተራማጅ እርምጃዎቹን መቃወም ነው።ያዲሞክራሲያ ከሃዲዎች ባለፉት ሁለት ዓመታት ያካሄዱት ትግል እንደዚሁ በደርጉ የወላዋይነትና አድሃሪ እርምጃዎች አያሳበቡ የደርጉን ተራማጅ እርምጃዎች በመቃወም ላይ ያተኰረ ነበር::ይህም፣በደርጉና በሕዝቡ መሃል ባለው ቅራኔ ላይ ብቻ በማተኰር በደርግና በሕዝብ ጠላቶች መሃል ያለውን ቅራኔ አዘናግቶ ሰፊው ሕዝብ ከፀረ ደርግ ጠላቶች ጋር እንዲጓበስ ለማድረግ ነበር::

ከላይ የጠቀስነው የትግል ዘዴ ሌላ ዘርፍ፣በቢሮክራሲውና በአንዳንድ የደርግ አድሃሪ አባሎች የሚወሰዱ አድሃሪ ድርጊቶችን በማእከላዊው ደርግ የተወሰዱ በማስመሰል የሚያደርጉት ቅስቀሳ ነው::እርግጥ ደርጉ ቢሮክራሲው ሆነ አድሃሪ አባሎቹ በሚወስዱት አድሃሪ እርምጃ ላይ ተገቢና ቆራጥ እርምጃ በማይወስድበት ወቅት ለድርጊቱ ተጠያቂ ነው::ቢሮክራሲው የሚፈጽማቸው ሁሉ የደርግ እርምጃዎች ብለው ከተወሰዱ ደግሞ በደርጉና በቢሮክራሲው መሃሉ ቅራኔ እንዳለ መካድ ነው::በደርግና በቢሮክራሲው መሃል ያለውን ቅራኔ መካድ፣ ደርጉ በቢሮክራሲው ላይ እርምጃ ለመውሰድ ያለውን ቸልተኝነት መታገል አይደለም::ቢሮክራሲው በሚያካሄደው ፀረ ደርግና ፀረ አብዮት ሴራ ተባባሪነትን የሚያስከትል ነው::ቢሮክራሲው የሚፈልገውም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ልክ እዚህ ወጥመድ ውስጥ እንዲገባለት ነው:: በቢሮክራሲው አሻጥር የሚፈፀሙ ድርጊቶች ሁሉ የደርጉ እንዲመስሉ፣ከደርጉ ''አስተዳደር አለመቻል'' የመጡ እንዲመስሉ ነው::ሰፊው ሕዝብ የትግሉ እንቅፋት ቢሮክራሲው መሆኑን ተረድቶ እንዳይታገለው፣ዓይኑን ከቢሮክራሲው ወደ ደርጉ እንዲያዞርለት እርሱም ፋታ አግኝቶ የሚከተለውን ፀረ ደርግና ፀረ አብዮት ሴራ ይበልጥ እንዲያፋፍም ነው::''ተፈሪ ማረኝ የደርጉስ ነገር ምንም አላማረኝ'' እንዲባለለት ነው::ደርጉን ለመክዳት በኢምፔሪያሊስቶች ሆነ በፊውዳሎች የታጨው የቢሮ ከበርቴው ስለሆነ፣በደርጉና በቢሮክራሲው መሃል ያለውን ቅራኔ ሳይረዳ ሰፊው ሕዝብ ቢሮ ከበርቴውን ትቶ ደርጉ ላይ ሲነሳ፣ጠላቶች ደርጉን ለመጣል የሚያደርጉትን ትግል አገዘላቸው ማለት ነው::እነ'ኢህአፓ'ም፣የቢሮክራሲውን አሻጥሮችና አድሃሪ እርምጃዎች በደርጉ የተወሰዱ አስመስለው ሲያቀርቡ ይህንኑ ግብ ለመምታት ነው::

እንግዲህ፣የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጠላቶች ''ተራማጅ ኮከብ'' የሆነው 'ኢህአፓ' ባለፉት ሁለት ዓመታት ከላይ ባጭሩ ለማስቀመጥ እንደሞከርነው ሕዝቡን መስሎ በሰፊው ሕዝብ ትግል ውስጥ በመግባት ባንድ በኩል የሕዝቡን ትግል ከውስጥ ሆኖ ለማዳከም፣በሌላ በኩል የሕዝቡ ትግል ከጠላቶቹ ጋር የሚያስለፈው አቅጣጫ እንዳይዝ ከፍተኛ ትግሎች አካሂዷል:: በዚህም ፀረ አብዮት ትግሉ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ጠላቶች ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቷል::ሌላ ሌላውን የተከፈለውን ወሮታ በርግጥ ባናውቅ እንኳ በፊውዳሎች በነመንገሻ ሥዩም ''እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች'' እንደአፍሪካ እዚ ባሉ የሲአይኤ ጋዜጦች ''ኢትዮጵያን ከወደቀችበት የፋሺስት ሥርዓት ለማውጣት የሚታገል ግንባር ቀደም ድርጅት'' እየተባለ ይሞካሻል::

'ኢህአፓ' በሕዝብ ጠላቶች ዘንድ ተወዳጅነት እያተረፈ ይሂድ እንጂ፣በአንፃሩ ደግሞ እንኳን ድርጅቱንም አጠገባቸው ባላደረሱት ጭቁኖች ዘንድ፣ወዳጅ መስሎ ያወናበዳቸው ሃቀኛ ዜጎች ባይቀሩ እየነቁበትና እያጋለጡት መጥተዋል::የኢትዮጵያን ጭቁኖች ከጠላቶቻቸው ጋር ለማስተባበር ያደረገው ትግል እስካሁን የአብዮታዊውን ትግል ከከፍተኛ ደረጃ መድረስ ካደናቀፈ ምክንያቶች አንዱ ቢሆንም፣ከእንግዲህ በሰፊው ሕዝብ መሃል 'በውስጥ አርበኝነት' ለአብዮት ጠላቶች የሚያገለግል ድርጅት መሆኑ እየታወቀበት መጥቷል::

'ኢህአፓ'ን ያከሰረት፣በፀረ ሕዝብነቱ እርቃኑ ሰንጋውን ያስቀረት ምክንያቶች ሃቀኛ ተራማጆች ከዚህ ቡድን ጋር ያካሄዱት ጽኑ የርእዮተ ዓለምና የፖለቲካ ትግል ብቻ አይደሉም::ባንድ ፊት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል መስመር እየያዘና የመደብ አሰላለፉም እየጠራ መምጣት፣በሌላ በኩል ደግሞ የደርጉ የራሱ ወገን መለየትና ከሞላ ጎደል ሳይንሳዊ ፈለግ የተከተለ የፖለቲካ መስመር መያዝ ነው::

በተለይ ከጥቂት ወራት ወዲህ ለአብዮቱና ለሃቀኛ ተራማጆች ምቹ እየሆነ የሚሄድ አካባቢ እየተፈጠረ ነው::በተከታታይ፣በደርጉና በሕዝብ መሃል ያለውን ቅራኔ የሚያለዝቡ፣ በደርጉና በሕዝብ ጠላቶች መሃል ያለውን ቅራኔ የሚያከሩ እርምጃዎች ተወስደዋል::የመለስተኛ ፕሮግራሙ መታወጅ፣የዲሞክራሲ ጮራ መፈንጠቅ፣የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የፖሊሲው ዕቅኔ መውጣት ...እነዚህና የመሳሰሉት ከላይ ያልነውን ሀቅ የሚያረጋግጡ [illegible]

ናቸው፡፡ለዚህም ነው ሃቀኛ ተራማጆች፣አንዳንድ የደርጉን አድሃሪ እርምጃዎችና ወላዋይነት ከማጋለጥ ሳይቆጠቡ፣እነዚህን ተራማጅ እርምጃዎች በመደገፍ ሊጠቀሙባቸው የሚታገሉት፡፡ ሰፊው ሕዝብም እነዚህን ተራማጅ እርምጃዎች በልዩ ልዩ መንገዶች ደግፏል፣እየተጠቀመባቸውም ነው፡፡ የነዚህ እርምጃዎች ተቃናሚ ሆነው የቀረቡት የለየላቸው የሕዝብ ጠላቶች ብቻ ናቸው፡፡ የዲሞክራሲያ ከሃዲ ቡድንም ከሕዝብ ጠላቶች ጋር እነዚህን ተራማጅ እርምጃዎች ተቃውሟል፣ከአድሃሪያት ጋር ተዳብሎም እንዲቀለበሱ እየታገለ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ከላይ እንዳልነው፣ለሃቀኛ ተራማጆችና ለአብዮቱ ይበልጥ ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ለከሃዲዎቹ ግን ''ከመለስተኛ ፕሮግራሙ /እነርሱ 'ከጥሪው ወዲህ' ነው የሚሉት / ወዲህ ያለው ፋሺዝም ይውደም'' ያሰኛቸው ሁኔታ መጥቷቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጭቁኖች በጠላቶቻቸው ላይ ለከፈቱት ጦርነት የበለጠ እንዲዘጋጁ የሚያመቻቸው እርምጃዎች በተወሰዱ ቁጥር፣የደርጉን ከቀላል ጉደል ባሁን ወቅት ከሰፊው ሕዝብ ጉን መሰለፍ የሚያሳዩ እርምጃዎች በተወሰዱ ቁጥር በዲሞክራሲያ ግንባር ቀደምነት ለሚመራው የከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች ጥርቅም ''ፋሺዝም'' የመፋፋሙ ምልክት ነው ማለት ነው፡፡ከመለስተኛ ፕሮግራሙ መውጣት ወዲህ ስለተፈጸሙ ''ፋሺስታዊ'' ድርጊቶች አንዱን ሲጠቅስ ዲሞክራሲያ በኪነት ሰራተኞች ላይ የደረሰውን ያመለክተናል፡፡

መለስተኛ ፕሮግራሙ በቀረበ ማግስት መሆኑ የአጋጣሚ ነው? ዝብሉ ቢያስጠይቅም፣ የኪነት ሠራተኞች ተገቢ ጥያቄ ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡ሰፊውን ሕዝብ ተታኙ የራሱን ቀልባሽ ጥያቄዎች ማስተጋባት ዋና ሥራው የሆነው 'ኢህአፓ' ጥቂት የተወና በዱና ከሃዲ ወጣቶችና በዘኔዎች ተጠቅሞ ሰልፉ ውስጥ ማደባለቁም አይዘነጋም፡፡በዚህም፣ የኪነት ሠራተኞችን ሰልፍ ለራሱ ቀልባሽ ዓላማ ለማዋል ባደረገው ሙከራ በነርሱ ላይ ለተወሰደው እርምጃ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የትግል ዘዴውም ሠራተኛውን አስገድሎ ''ይሽውላችሁ ፋሺዝም'' ለማለት ስለሆነ፣በመጠኑ ተሳካለት፡፡ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ከወታደሩ በተተኮሰ ጥይት ሰርጉ ገቡ ''የኢህአፓ' ከሃዲ ሠራዊት ሳይሆን አንድ ንፁህ ሠራተኛ ወደቀ፡፡ የ'ኢህአፓ' ዓላማ ለሰራተኛው ለመቆም ሳይሆን አስገድሎ ለመሸሸ፣በዚህም የ''ፋሺዝምን'' መኖር ለማሳየት ስለሆነ የሞተው ንፁህ ሰራተኛ እንጂ የ'ኢህአፓ' ደጋፊ አለመሆኑ የሚያስገርም አይደለም፡፡ ለማንኛውም ተገቢ ጥያቄ ቢቀርቡ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ጥይት መተኮስን ማንኛውም ተራማጅ ያወግዘዋል፣እጃቸው ያለበት ሁሉ በሕግ ሊጠየቁበት ይገባል፡፡ 'ኢህአፓ' ግን አንድ ሰው ብቻ በመገደሉ የከነከነው ይመስላል፡፡ የፈለገው የሸርፕቪለን ዓይነት ጭፍጨፋ ነበር፡፡ በጋዜጣውም በሃቅ የነበረውን ሳይሆን በምኞቱ የነበረውን ሲገልጽ ''የሸርፕቪል ዓይነት ግድያ'' ይለዋል፡፡ የሸርፕቪል ጭፍጨፋ፣ መቶ ግድም የአዛንያ አፍሪካውያን በፋሺስቱ መንግስት ወታደር የተገደሉበት ጭፍጨፋ ነበር፡፡ ታዲያ በኪነት ሠራተኞች ላይ የተወሰደው እርምጃ በፈለገው ማይክሮስኮፕ ጉልቶ ቢቀርብ ሸርፕቪልን ሊሆን አይችልም፡፡ 'ኢህአፓ' የፈለገው የሸርፕቪሉን ዓይነት ጭፍጨፋ እንደነበረ ነው የሚገልጸው፡፡ ለወደፊቱም፣ የ'ኢህአፓ' ደጋፊዎች እየተነኮሱ ሠርተአደሩን ማጋፈጥ ዓይነተኛ የትግል ዘዴያቸው ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ወዛደሮችና ሠርቶ አደሮች ሁሉ በሰርጉ ገቦች ተገፋፍተው ባልተዘጋጁበት ትግል እየተጋፈጡ የአናርኪስቶች መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ነቅቶ መጠበቅ ሃላፊነታቸው ነው፡፡

ሌላ ምሳሌ ለመጨመር ያህል፣ደርጉ ስለኤርትራ ጉዳይ ያሳለፈውን የግንቦት 8 የፖሊሲ ውሳኔ እንመልከት፡፡ የዚህን ውሳኔ መውጣት፣ለኤርትራ ችግር ዘረውኑ መፍትሄ በማስገኘቱ ሳይሆን፣ የኤርትራን ችግር ለመፍታት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፣ማንኛውም ሃቀኛ ተራማጅ እንደሚደግፈው በዚሁ ጉዳይ ላይ ባወጣነው የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ልዩ እትም ላይ ገልፀናል፡፡ውሳኔው ለኤርትራ ችግር መፍታት ጥርጊያ መንገድ የሚከፍት በመሆኑም የኤርትራና የኢትዮጵያ ጭቁኖች ድጋፋቸውን ገልጸዋል፡፡ከኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶችና ከኤርትራ አድሃሪዎች ጉን በመሰለፍ የ'ኢህአፓ' ከሃዲዎች ይህን ውሳኔ ተቃውመው ''ተራ ማጭበርበሪያ''፣ ''አንካሳ መፍትሄ''፣ ''ቅንነት የለሽ መፍትሄ'' ይሉታል፡፡/ዲሞክራሲያ፣ ቅጽ 3 ቁጥር 5፣ገጽ 4/ የኤርትራ ችግር በሰላማዊ መንገድ መፈታት የኢትዮጵያና የኤርትራን ጭቁኖች አንድነት መፍጠርና በሕብረት በደመኛ ጠላቶቻቸው ላይ መዝመትን ያስከትላል፡፡ የደርጉ የፖሊሲ ውሳኔ ለዚሁ ግብ ትልቅ ጥርጊያ መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶችና የኤርትራ አድሃሪዎች የሚፈልጉት ደግሞ ጦርነቱ እንዲቀጥል፣የጭቁኖች አንድነት እንዳይፈጠርና በነርሱ ላይ እንዳይዘር ነው፡፡ የበኩር ልጃቸው 'ኢህአፓ' በዚህ ጥያቄ የፖሊሲ ውሳኔውን ተቃውሞ ከነርሱ ጉን በግልጽ ቆሟል፡፡

ያም ሆነ ይህ፣'ኢህአፓ' ሰፊውን ሕዝብ ከጠላቶቹ ጉን ለማሰለፍ ያደረገቸው ሙከራ እየከሸፈ መጥቷል፡፡ከንግዲህ የሕዝብ ወገን መስሎ ማወናበዱ አከትሟል፡፡ ትግሉ እየከረረና እየጠራ ሲመጣ፣ኢህአፓ በሕዝብ ፊት ለሚደርስባት መጋለጥ በአብዮት ጠላቶች ታዝላ እሽሩሩ ስትባል፣አንዳንዴም ከአቀፍ ዐርዳ ለፋሺስታዊ ቀልበሳ በገቢር የሚጠቀሙ ቅስቀሳዎች ስታካሂድ ነው የምታጋጥመን፡፡

እንግዲህ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በራሳቸው የተጥቀ ትግል እየከሰሩ ሲመጡ፣ ሕዝቡን ለማወናበድ ያካሄዱት ፕሮፓጋንዳ ጥጋ ቢስ እየሆነ ሲሄድ፣ ሕዝቡ ውስጥ አስርገው ያስገቡት 'የውስጥ አርበኛቸው' እየተነቃበት ሲሄድ፣ ሥልጣን ላይ ለመመለስ ያላቸው አማራጭ በፋሺስታዊ የመፈንቅለ መንግሥት አማካይነት ይሆናል። ባለፈው ወር ቍጥር የከሸፈው ፋሺስታዊ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የሚያንፀባርቀው ይህንኑ ነው። ሙከራው ባሁኑ ጊዜ የተደረገው፣ ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል አድሎ ጠላቶችን ከመቸውም ይበልጥ ያበደነገጠበት ደረጃ መድረሱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፊተ ማወናበጃ ፕሮፓጋንዳ ሁሉ ተቀባይነት ማጣቱና ጠላቶቻችን ሥልጣን ላይ ለመመለስ የቀተና የመረተ ትግል ማካሄድ ያለባቸው ዛሬ መሆኑ ገልጽ ስለሆነ ነው።

በሽለቃ ሲሳይና በጄኔራል ጌታቸው መሪነት የቍከረው ይህ ፋሺስታዊ የመንግሥት ገልበጣ፣ በጥቂቶች የተወጠነ ተራ የኩዴታ ሙከራ አልነበረም። ከሲአይኤ፣ ከኢትዮጵያ የቀድሞ መሳፍንትና ከበርቴዎች፣ እንዲሁም ከሌሎች አድሃሪ ኃይሎች ጋር ሁሉ በመተባበር የተዘጋጀ ወጥን ነበር። ሙከራው የከሸፈው በአጋጣሚ እንጂ በሙከራዎቹ በኩል የተደረገው ዝግጅት ቀላል ሆኖ አልነበረም። ወታደሩን ለመከፋፈል ከፍተኛ ሴራዎች ተካሂደዋል። ሁኔታውን ለኩዴታ ለማመቻቸት ትላልቅ የኢኮኖሚ አሻጥሮች እንዲፈፈሙ ተደርገዋል። የሚገዙ ኃይሎችን ለመግዛት ብዙ ሚሊዮን ዶላር ተመድቧል። በቀምባሳ ወደብና በቀይ ባህር አካባቢ በዚያን ሰዓት አውሮፕላን ተሸካሚ የጦር መርከቦች የተሰማሩት አሳ ለማጥመድ አልነበረም። በፕሮፓጋንዳ ደረጃም፣ በለደርጉ 'የምርጥ መኰንኖች መንግሥት መሆን'፣ 'የኢትዮጵያ ጭፍን ወታደሮች ተባብረው ይህን 'የምርጥ መኰንኖች መንግሥት' መጣል እንዳለባቸው፣ በጠቅላላው ዓላማቸው 'ኢትዮጵያን ከውድቀት ለማዳን' በለመሆኑ፣ ወረቀት በመበተንና በማስወራት ትልቅ ፖለቲካዊ ዝግጅት አድርገዋል። በገቢር ለፋሺስታዊ የመንግሥት ገልበጣዎች ሁኔታውን ለማመቻቸት የሚታገለው 'ኢህአፓ' የበኩሉን ሰርቷል። ባንድ በኩል ወዛደሩ ሠራተኛው በተናጠል የሥራ ማቆም አድማዎች እንዲወርድ፣ አርሶአደሩ እንዳያርስ፣ ምርቱን እንዳይሸጥ ለማድረግ ጥረቱን አፋፍሞ ነበር። በሌላ በኩል፣ የደርጉ መለስተኛ ፕሮግራም የጠቀሰው የኢትዮጵያ ሕዝቦች እራሳቸው ተደራጅተው በወዛደሩ ፓርቲ መሪነት የሚያቋቁሙትን አብዮታዊ ግንባር ሆኖ ሳለ፣ ይህንን ያልተረዳ በመምሰል፣ እነዚህ ፋሺስታዊ የመንግሥት ገልበጣ ጠንሳሾች ሊጠቀሙበት ያቀዱት 'ግንባር' ቅስቀሳ ሲያካሂድ ነበር።

ባጭሩ፣ የነሲሳይ የመንግሥት ገልበጣ ሙከራ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በሙሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የተካፈሉበት፣ ከፍተኛ ዝግጅት የተደረገበት ሙከራ ነው። እንደ ገመትነው፣ የከሸፈው በአጋጣሚ እንጂ በዝግጅቱ አነስተኛነት አልነበረም። የነሲሳይ ሙከራ መክሸፍ ግን በአገራችን ፋሺስታዊ የመንግሥት ገልበጣ ሙከራዎች ከንግዲህ አይኖሩም ማለትን አያበስርም። የመንግሥት ገልበጣ ሙከራ ከንግዲህ ከነጭራሹ ሊጠፋ ይቀርና ይህናው የነሲሳይ ሙከራ እንኳን ከላይ ተቆጪ እንጂ እስከታች ድረስ ሙሉ በሙሉ አልተመታም። ለብዙ ዓመታትና በብዙ አገሮች የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎችን የመራው ሲአይኤ በአንድ ሙከራ መክሸፍ ተስፋ የሚቆርጥ አይደለም። በአንድ ጊዜ እንኳን የሚያዘጋጀው በርከት ያሉ አማራጭ ሴራዎችን ነው። አንዱ ሲከሽፍ ሌላውን ለመሞከር። ስለዚህ፣ ፋሺስታዊ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች አደጋ ዛሬም አልተወገደም። ወደፊት ሊመጡ የሚችሉት የገልበጣ ሙከራዎች እንደ ነሲሳይ ሙከራ ሁሉ ይከሽፋሉ ወይንም ሥራ ላይ ሳይውሉ ይነቃባቸዋል ማለት ደግሞ እጅግ ተሳስሮ እራስን ለሞኝነት ማስረከብ ነው። ከነሲሳይ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለው የቀልበሳ ሙከራ ከዚህኛው የበለጠ ዝግጅትና ጥንቃቄ እንደሚኖረው ሳይታለም የተፈታ ነው። በአንፃሩም፣ በጭቁኖች ወገንም የቀልበሳ ሙከራዎችን ለማክሸፍና አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ ከመቸውም የበለጠ ዝግጅት መደረግ ይኖርበታል።

ባሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የተደረጉ ወይም የሚደረጉ የቀልበሳ ሙከራዎች ሁሉ የቅርብ ጊዜ ዓላማቸው ደርግን ለመጣል ቢሆንም መሰረታዊ ግባቸው የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ባጭሩ ለማስቀረት ነው። የቀልበሳ ሴራዎች ፀረ ደርግ ብቻ ሳይሆኑ ፀረ አብዮት ጭምር ናቸው። አብዮቱን ከቀልበሳ መጠበቅ የደርግ ተግባር ብቻ ስላልሆነ፣ ወታደራዊው ደርግ እነዚህን የቀልበሳ ሙከራዎች ለማክሸፍ ሰፊው ሕዝብ ተካፋይነት እንዲኖረው ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ አለበት። ባለፈው የመንግሥት ገልበጣ ሙከራ ተካፋይ ሆነው ያመለጡ ግለሰቦችን እንዲከታተል ሰፊው ሕዝብ መጋበዙ ለዚህ ተካፋይነት በቂ አይደለም። ደርጉ፣ እንኳን ሕዝቡ የቀልበሳ ሙከራዎችን ለመመከት በሚደረገው ትግል የሚሳተፍበትን እርምጃ ሊወስድ፣ ስላለፈው ፋሺስታዊ የመንግሥት ገልበጣ ሙከራ ለሰፊው ሕዝብ በቂ ገለጣ አላደረገም። ሌላው ቀርቶ፣ የሲአይኤ እጅ እንደነበረበት በተዘዋዋሪ መንገድ እንኳ አልተገለጠም። ለጥቂት ስለ ከሸፈው ሴራ በቂ ገለጣ ስላልተደረገለት፣ ሰፊው ሕዝብ አብዮቱን ለመቀልበስ የታቀደውን የነሲሳይ ሙከራ የሚሰጠው በቀላል ግምት ነው። በራሱ አብዮት ላይ የተጠነሰሰውን ከባድ ፀረ ሕዝብ ሴራ በቀላሉ መገመቱ ደግሞ ሌሎች ሴራዎችን ለመመከት ማድረግ ካለበት ከፍተኛ ዝግጅት የሚያዘናጋው ነው።

ወታደራዊው ደርግ፣ የቀልበሳ ሙከራዎች ማክሸፍን የራሱ ተግባር ብቻ አድርጎ እስከወሰደ ድረስ፣ የሠራዊቱን ምንነት በራሱና በፀጥታ ከፍሉ ኃይል ብቻ እስካስቀረ ድረስ፣ እንኳን የቀልበሳ አደጋን ሊደመስስ፣ የቀልበሳ ሙከራዎችን በበለጠ ይጋብዛል፡፡ ሰፊው ሕዝብ የቀልበሳ ሙከራዎችን ለማክሸፍ በሚደረገው ትግል ሙሉ በሙሉ ለበቂ ተባተፈ ድረስ፣ ወታደራዊው ደርግ ከሰፊው ሕዝብ ተገንጥሎ "እኔው አውቅልሃለሁ" እስካለ ድረስ፣ ቀለባሾች አንዱ ሙከራቸው ሲከሽፍ ከቀጣዩ ሙከራዎቻቸው በአንደኛው እንደሚያሸንፉ ያውቃሉ፡፡ የፀጥታ ድርጅቶች ክትትል የአጋጣሚ እንጂ ዋስትና ያለው የፀረ አብዮት ሴረኞች መደምሰሻ አይደለም፡፡ ዋስትና ያለው የቀልባሾችን ሴራ መደምሰሻ የሰፊው ሕዝብ የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ኃይል ብቻ ነው፡፡

ስለዚህም፣ በአገራችን ፀረ አብዮት ቀልበሳን ለመቋቋምና በመጨረሻም ላለማስቻል የሰፊው ሕዝብ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ እጅግ አጣዳፊ ጉዳይ ነው፡፡

በማንቃት ተግባር፣ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን ማስተማር ብቻ በፍፁም በቂ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ መታወቅ አለበት፡፡ በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ የመደቦች አሰላለፍ በሚገባ መታወቅና ሕዝቡ ወዳጅና ጠላቱን ጠንቅቆ እንዲረዳ ማድረግ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት የውስጥና የውጭ ጠላቶች የሚጠቀሙትን ሴራ በተጨባጭ መንገድ በሚገባ ማብራራትና ሰፊው ሕዝብ የሚዘጋጁበትን ፀረ አብዮት አመጽ ጠንቅቆ በማወቅ አፀፋውን ለመመለስ እንዲዘጋጅ ማገዝ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ የነሲሳይን የቀልበሳ ሙከራ በመረኩዝ ቀስቃሽ ፀረ አብዮት ኃይሎች ለፋሺስታዊ የመንግስት ግልበጣ ተሸቀ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው በሰፊው መገለጽ አለበት፡፡

በሌላ አንፃር፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ወታደሮችና ተራማጅ መኩንኖች ከጭቁኖቹ ጎን ተሰልፈው ለመሠረት እንቅስቃሴ እስካሁን ታማኝ ሆነው ቆይተዋል፡፡ በነሲሳይ የመከፋፈል ሙከራ ያለመፈታታቸው ብቻ ሳይሆን የነሲሳይን ገብረ አበሮች በመደምሰስ የወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ለዚህ ምስክር ነው፡፡ የሆነ ሆኖ፣ እነሲሳይ እንዳደረጉት ሁሉ፣ የሚቀጥሉት የቀልበሳ ሙከራዎች የሚያተኩሩት ወታደሩን በመከፋፈል ላይ ነው፡፡ ስለዚህም፣ አድሃሪዎች ወታደሩን ለመከፋፈል የሚያደርጉት ሙከራ እንዲከሽፍ፣ በማንኛውም ሁኔታ ጭቁን ወታደሮችና ተራማጅ መኩንኖች ከጭቁኖች ጎን በመሰለፍ ፀንተው እንዲቆሙ የአድሃሪዎችን ሴራ ለነርሱም ማሳወቅና የፖለቲካ ንቃታቸውን ከፍ ማድረግ ከጊዜው አጣዳፊ ተግባሮች አንዱ ነው፡፡

ድርጅታዊ ዝግጅትን በሚመለከት በኩል፣ አሁንም የወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር የኢትዮጵያ አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው፡፡ ሰርጎ ገቦችንና በወዛደሩ የቃያ ማህበር አመራር ላይ የተሰገሰጉትን ቀልባሽ አናርኪስቶች በማጋለጥ የተደረገው ትግል ብዙ ድሎች በማቀዳጀቱ በወዛደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን ለማስፋፋት፣ ከንቁ ወዛደሮች ፓርቲ የትግል ሕብረት ለመፍጠር እስከቀርብ ጊዜ ድረስ ያልነበረ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሌላ አነጋገር የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ለሚደረገው ትግል የፀና መሰረት ተጥሏል፡፡ እንግዲህ የወዛደሩን ፓርቲ መመስረተን እንደአላማቸው አርገው የወሰዱ ሃቀኛ ማርክሲስቶች ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አንድነታቸውን ገንብተውና ኃይላቸውን አስተባብረው መታገል አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት የሩቅ ጊዜ ገብ ሆነ የቅርብ ጊዜ ዕድል የተያያዘው ከወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር ጋር ነው፡፡ ስለዚህም፣ የወዛደሩ ፓርቲ መፈጠርና አለመፈጠር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በመረዳት የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች በዚህ ጉዳይ ያለባቸውን ከባድ ሃላፊነት ተረድተው ለወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር ሌት ተቀን መታገል አለባቸው፡፡

የአርሶ አደሩ ማህበራት፣ የዛሬውን አብዮታዊ ትግል ለማራመድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ባንድ በኩል የተራማጅ ዘማቾች መመለስ፣ በሌላ በኩል የአድሃሪ ቢሮክራቶች ቁጾችና እነዚህን ማህበራት እንዳያዳክም፣ የአርሶ አደሩን ትግል ለማገዝ የተሰለፉ ተራማጅ የመሬት ይዞታ ሠራተኞችና አስተዳዳሪዎች ከመቸውም የበለጠ ከአርሶአደሩ ጎን መቆም አለባቸው፡፡ ደርጉም ቀን በቀን ከአርሶአደሩ ጋር የሚፋጠጡ አድሃሪ አስተዳዳሪዎችንና ቢሮክራቶችን በማንሳት በተራማጅ አስተዳዳሪዎች መተካት አለበት፡፡ የገበሬ ማህበራት መጠናከር ቁርጥ መዳከም፣ በየቦታው የተፋፋመው የመሬት ከበርቴዎችን ፀረ አብዮታዊ አመጽ የበለጠ የሚያበረታታ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በዚያው መጠን ደግሞ፣ በመንግስቱ የመገናኛ ዘዴዎች ጥምር እየተጠቀሙ በልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ቋንቋ ቀስቀሳ በማድረግ የአርሶአደሩን ንቃት ማሳደግ የተራማጆች ሁሉ ግዴታ ነው፡፡

የትጥቅን ጥያቄ በሚመለከት በኩል፣ የቀልበሳ ሙከራዎችና ባጠቃላይ የፀረ አብዮት ኃይሎች ትግል መፋፋም የሰፊውን ሕዝብ መታጠቅ ጉዳይ እጅግ አጣዳፊ አድርጎታል፡፡ ከላይ እንዳልነው ሁሉ፣ ደርግ የቀልበሳና የመንግስት ግልበጣ ሙከራዎችን ለማክሸፍ "እኔ እበቃለሁ" እስካለ ድረስ በገቢር የቀልበሳና የግልበጣ ሙከራዎችን መጋበዙ ነው፡፡ እንዲሁም፣ ያልታጠቀን ሕዝብ በታጠቁ ኃይላቸው ማሸነፍ እንደማያቅታቸው አድሃሪዎች ጠንቅቀው

ያውቃሉ::ስለዚህ፣በሰበብ በአስባቡ የሰፊው ሕዝብ ገ ታጠቅ እስከዛሬ ድረስ የቀለበሳና የመንግስት ግልበጣ ሙከራዎች በሙሉ ድፍረት ይዘጋጃሉ::ይህም በዘዋዋሪ መንገድ የቀለበሳና የግልበጣ ሙከራን መጋበዝ ነው::ስሌንኳ:ሰፊውን ሕዝብ ለማስታጠቅ በመወላወሉ የከፈለው ቅጣት ሰደርግና ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ትምህርት ሊሆን ይገባል::

ለማጠቃለል ያህል፣የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ማየል የጠላቶቻችንን የቀለበሳ ዝግጅት አፋፍሞታል::በነሲባይ የተሞከረው የመንግስት ግልበጣና የአብዮት ቀለበሳ ሴራ ቢከሸፍም፣የቀለበሳ ሴራ ለዘላለሙ ጠፋ ማለት አይደለም::እንዲያውም የሴራ ሙከራዎች ወደፊት ይመጣሉ::ወታደራዊው ደርግ በአጋጣሚ ካልሆነ እነዚህን ሙከራዎች እስከመጨረሻው ሊመክት አይችልም::አብዮት ደግሞ በመደበኛ ትግል ሕግ የሚመራ እንጂ በአጋጣሚ ላይ ተማምኖ የሚራመድ ነገር አይደለም::ስለዚህ፣አብዮታችንን ከቀለበሳሊያድነንና ከግብ ሊያደርስ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ የነፃ፣የተደራጀና የታጠቀ ኃይል ብቻ ነው::

የሩሲያ ጭቁን ሕዝቦች ከ1905 እስከ 1907 ያደረጉት አብዮታዊ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለፉት ሁለት ዓመታት ካደረጉት ትግልጠለጠ እንጂ የሚያንስ አልነበረም::ሆኖም የሩሲያ ጭቁኖች በዚያን ጊዜ ያካሄዱት የሁለት ዐመት ትግል በበቂ የነፃ፣የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ ትግል ሊሆን ስላልቻለ በአድሃሪያኖች አሸናፊነት አከተመ እንደጋና የ10 ዓመት ፋሺስታዊ አገዛዝ በሩሲያ ሕዝቦች ላይ ሰፈረ::ተከፋ ለማስቀረት ሳይሆን፣ያለብንን ከባድ ሃላፊነት ለመሸከም እንድንችል የኢትዮጵያ ጭቁኖችም ትግል ከተመሳሳይ ፈተና ላይ መሆኑን መረዳት አለብን::አብዮታችን የነፃ፣የተደራጀና የታጠቀ ጎዳና እስካልያዘ ድረስ የቀለበሳ አደጋ እየጨመረ የሚሄድ ነው::ስለዚህ፣የሰፊውን ሕዝብ ንቃታዊ፣ድርጅታዊና ትጥቃዊ ዝግጅቶች በፍጥነት አሟልተን ጠላቶቻችንን ለአንዴና ለሁልጊዜ ለመደምሰስ ከመቸውም የበለጠ እንነሳ!!

የአድሃሪያኖች የቀለበሳ ሴራ ይወድማል!!

የነፃ፣የተደራጀና የታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ያሸንፋል!!